# ነጻነቱን አጥቶ




**(መይሳው ከምድረ ስዊድን)**

ፍቅር ከምድር ጠፍቶ- ሰው ለሰው ልጅ ከፍቶ፣

ያሸተው እያረረ - የሚሰማው ጠፍቶ፣

ሁሌ እንዳዘነ - እንደተማረረ፣

ሞት እየነጠቀን - ግዜው እየበረረ፣

አፈር ይበለዋል - እንጀቱ እንዳረረ፣

መቼ አንጠረጠረ - መገንዘብ ተስኖት፣

ከድቅድቅ ጨለማ - ገብቶ ከጥፋት፣

መልሶ መላልሶ - እየሰራ ክፋት፣

ካዙሪት ውስጥ - ገብቶ፣

በቁመናው - ሞቶ፣

ስህተቱን ሳያርም - ሁሌ እየዋተተ፣

ማስተውል ተስኖት - የሰው እየደረተ፣

ከታላላቆቹ - አልማርም ብሎ፣

ሸክም ተሸክሞ - ተራራ ቆልሎ፣

ቀላዋጭ ከሆነ - ባሕሉን ካልጠበቀ፣

ለሃገሩ ክብር - ካልተጠነቀቀ፣

እንዲሁ ይቀራታል - እንደተቀመጠ፣

የራሱን ካልያዘ - የሰው ከቋመጠ፣

ባዕድ ይበላዋል - እየመጠመጠ።

ቁልቁል ከወረደ - አገር ሰሚ አጥቶ፣

መናገር ተስኖት - እንደበቱን ዘግቶ፣

ናባዛ ከሆነ - በቁሙ ያልታደለ፣

አቅማዳውን - ይዞ ነጩን ከለመነ፣

ከዘመኑ ጋራ - መቼ አብሮ ዘመነ፣

ምጽዋት ከጠየቀ- ሰርቶ ካላደረ፣

ያባቶቹን ክብር - ጠብቆ ካልኖረ፣

የተሰናከለ - በሰው ላብ የሚያድር፣

ብኩን ሆኖ የሚኖር - ምግባሩ የማያምር፣
ሀፍረት ተሸክሞ - በምድር ላይ የሚኖር፣

የዓለም መሳለቂያ - ክብሩን ተቀምቶ፣

ሰው ሰው ይሆናል - ወይ ነጻነቱን አጥቶ።